# እንዘንጥ ለእየሱስና የነጻው ገበያ ጳጳስ

ከበልጅግ አሊ

ሰውየው ፍካሬ እየሱስን ቄሱ አንብበው ሲያስረዱት የስምንተኛ ሺህ መድረስ ምልክቶች ሁሉ የደረሱ ይመስለውና ሳልዘጋጅ ተያዝኩ ብሎ ለማንም ሳያማክር ጓዙን ጠቅልሎ መንኖ ገዳም ይገባል።ሴትየዋም ባሏ ሲሞትባት ሌላም ወንድ የምታፈቅር ወይም ከእሱ ሌላ ወንድ ያስጠላትና ለማንም ሳትናገር ሳታማክር ጓዟን ጠቅልላ ወደ ገዳም ትገባለች።

ግዜ እያለፈ ሰውየው የጠበቀው ስምንተኛ ሺህ ሳይደርስለት ሲቀር፣ ሴትየዋም ያ ትንገበገብለት የነበረው የባል ፍቅር እያደር እየቀነሰ ፣ ሃዘኑም እየጠፋ ሲመጣ አይን መንከራተት ይጀምርና ወጣቱ ሰውዬ ላይ ያርፋል። ወጣቱ ሰውየም ይህችን በወጣትነትዋ አለም በቃኝ ብላ የመነነች ወጣት ሴት ቀድሞውኑ ከአይኑ ገብታ ኖሮ ቀስ እያሉ ሰላምታ መቀራረብ ይፈጠራል። አይቀር የለ መቀራረብ መዋደድ ያመጣል። በሃይማኖት ፅናት ያልተጀመረ ሰለሆነ የጣር ዘመንን ማለፍ ያቅታቸውና ልጅ ይፀነሳል። ከገዳሙ ተወጥቶ ኑሮም ይጀመራል። ታዲያ የሚወለደውን ልጅ ስም ሲያወጡለት ፣ አንተ ባልከው፣በሱ ፍቃድ ብለው በእግዜር ያሳብባሉ ብሎ የተፃፈ ፅሁፍ ትዝ ይለኛል።

ሌላዋ አሮጊቷ ከጎረቤታቸው ሲጣሉ ለአካባቢያቸው ታቦት የሷን ነገር ያሳየኸኝ እንደሆን የአስር ሳንቲም እጣን አታጣም ብለው ይሳላሉ፣ጎረቤታቸውንም ያሳጣሉ። ለነገሩ ነገ ደግሞ ከጎረቤታቸው ሲታረቁ ሁኔታው ይረሳል።ለአሮጊቷ የግዜያዊ ንዴታቸውን መግለጫ ነው እንጂ እቃና የጎደለ ነገር የሚዋዋሱትን ጎረቤት ለሁል ግዜ ማጣት አይፈልጉም። ዛሬ ሃይማኖቱም ተለዋውጦአል። ስለቱም ሌላ ይዞታ ይዞ የግል ጥቅምን ማስፈፀሚያ ነው።በእንግሊዝ ሃገር ያለች አንዷት ወጣት በእንግሊዝ የመኖሪያ ፋቃዷ ከተሳካላት ለቁልቢ ገብርኤል ነፍስ ያላት አይጥ ይዛ እንድትሄድ ነው የተሳለችው ተብሎ ሲወራ ሰምቻለሁ። ነገሩን ልብ ብለን ስናጠናው በእንግሊዝ ሃገር ለአንድ ጠበቃ ከሚከፈለው ጋር ቁልቢ የሚገኘውን ስናወዳድረው ቁልቢ ይህንን ሁሉ ፈፅሞ የሚያገኘው ኪሳራ ብቻ ነው።ቢሆን እንኳ ቤተክርስትያኑና ምእመናን የሚመፀውቱትን በማመን በቤተከርስትያኑ አጥር ስር ለተኮለኮሉ  የኔ ቢጤዋች ለመርዳት የገንዘብ ሰጦታ ቢደረግ ይሻላል ብዬ አምናለሁ። ይህ ሁሉ እንግዲህ ሃይማኖቱን በጥልቅ አለማወቅ ነው።

በአለፈው ሰሞን ጎረቤቴ ይኖር የነበረ ወጣት መፀሃፍ ቅዱሱን ቀስሮ ወደኔ መጥቶ ኢየሱስን ካልተቀበልክ ብሎ ሲሞግተኝ ነበር የከረመው። ይህ የምነግርህ ቃል ከእየሱስ ለአንተ በኔ  ውስጥ የተላከ ነው።የኔን ወጣትነት አትመልከት እኔ የእየሱስ ቱቦ ነኝ። መልዕክቱን ማስተላለፍ ብቻ ነው። ቃሉ ግን የእየሱስ ነው። መምጫው ቀን ደርሶልና አስብበት ብሎ ሰውየውን ወደ ገዳም  እንዳስኮበለለው ቄስ ሞካከሮኝ ነበር። ስንት አመት ሙሉ ክርስትያን ነኝ ብዬ የማምነው ግለሰብ ዛሬ ስሞኑን አዲስ ሃይማኖት አግኝቶ ገና ፊርማው ባልደረቀ ወጣት እምለወጥም እንዳልሆንኩ እንዲያውቀው ብዬ  መፀሃፍ ቅዱስን ተቀብዬ ገልበጥ ገበጥ አድርጌ ስምለከተው በመካከሉ

„ ኤሎሄ አሎሄ ላማ ሰበቅተኒ“

የሚለውን አገኘሁና ወጣቱን ምን ማለት እንደሆነ ጠየቅሁት። መልሱን ሊገኝ አልቻለም።አንድ እየሱስን በሱ አስተሳሰብ ያልተቀበለ ሰው የጠየቀውን ጥያቄ መመለስ ስላቃተው መውጫ እንደሚፈልግ ተገንዝቤ ጨዋታውን ቀየርኩት። ለመሆኑ የጉዳይህን ነገር እንዴት ሆነ? ብዬ ጠየቅሁት።ታዲያ ወጣቱ አንድ ነገር ብሎ አሳቀኝ። የነፍሴን ከእየሱስ የስጋዬን ከቅንጅት ነው የምጠብቀው አለኝ። ነገሩ ገብቶኛል የስደተኛውን ጥያቄው ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ቅንጅትን ይፍታው ማለቱ ነው። ገፋ ብዬ ድሮ በወያኔ እንደሚናደድ ስለማውቅ አሁን  ስለወያኔ ምን ታስባለህ ብዬ ጠየቅሁት። ኢየሱስ መርጦ ያስቀመጠው ስለሆነ ልንቃወመው አይገባም አለኝ። ይሄ በልጁ ላይ ያየሁበት ታላቅ ለውጥ ነው።ያ በየሰልፉ የሃገሩን ባንዲራ አድርጎ የማይጠፋ ወጣት ዛሬ እንደዚህ አይነት ለውጥ ማምጣቱ በጣም ገረመኝ። ግን እንዴት ይህ ሊፈጠር እንደቻለም መገመት አያቅተኝም።

እስቲ እሁድ ለት እንደዚህ አይነት ወጣቶች ወደሚሰበሰቡበት አዳራሽ ሄዳችሁ ተመልከቱ። የአንዳንዶቹ አለባበስ ወደ ጸሎት ሳይሆን ወደ ዳንኪራ መጨፈሪ ቦታ ሊሄዱ የተዘጋጁ ይመስላሉ። ንጹህ ሆኖ መሄድ ሌላ መሽቀርቀር ሌላ። ይህን ሁኔታ የፀሎቱ ቤት ፓስተሮች በጣም የሚደግፉት ነው። ኮረዳዎቹን ለመፈለግ የሚመጣውን ጉብል የሚያጠምዱበት በወንፊት ስር ለወፍ የተበተነ እህል ነው።ይህንንም ወጣት ወደዛ ምን እንደሳበው ማወቅም አዳጋች አደለም።

በተለይ በውጭ ሃገር ያሉትን ስንመለከት አንድ የተሳሳተ ጉዳይ እንዳለ እናስተውላለን።የኑሮ ሁኔታ የከበዳት / የከበደው ፣ የፍቃድ ወረቀት የሌላት / የሌለው ይህንን ችግሩን ለማርያም ተስሎ /ተሰላ ካልተፈፀመለት / ካልተፈፀመላት የሚያደርገው / የምታደርገው ቢኖር ወደነ እንዘንጥ ለኢየሱስ አካባቢ መሄድ ነው።እንዘንጥ ለእየሱስ ለእንደዚህ አይነት ግለሰቦች የተሰጠ ስም ነው። አንድ ሁለቴ ከተመላለሰ / ከተመላለሰች ደግሞ ኢየሱስን ሊቀበል / ልትቀበል ነው ተብሎ እንክብካቤውን ሲያየው / ስታየው እዛው ሰምጦ / ሰምጣ ትቀራለች / ይቀራል። የወረቀት የመኖሪያ ወረቀት ችግር ያለባትን በትዳር ልትወጣው የፈለገችውም እነርሱ ጋ ሄደሽ አትፈልጊም እንዴ?የምን መንገላጀጅ ነው ስትባል ተሽቀርቅራ እዛው ጎራ ማለትዋ አይቀርም።እንግዲህ በተለያየ ምክንያት እዛ የተሰበሰቡት በሙሉ በየያሎት ቀኑ ተሽቀርቅረው ቢመጡ ምን የሚሰገርም ሊሆን ነው ስሙስ እንዘንጥ ለእየሱስ አይስማማቸውም ብላችሁ ነው። ይህም ቢሆን ሃይማኖቱን በደንብ አለማወቅና ለማይረባ ምክንያት መጠቀም ነው።

ዋናው ሃይማኖት ነውና ልንቃወመው አይገባም ልትሉኝ ትችላላችሁ ቢሆንም ሃይማኖትን ለማይሆን ጉዳይ የመጠቀም ጉዳይ ደግሞ ዝም ብለን ልናልፈው አይገባም።አንዳንድ የእዘንጥ ለእየሱስ አላፊዎች አባሎቻችውን ወያኔን መቃወም አያስፈልግም ምክንያቱም ስልጣን ላይ ያወጣው የመረጠው ጌታ ነው ስለሆነ ልንቃወመው አንችልም ብለው ወጣቶችን ለሃገራቸው እንዳያስቡ የሚደርጉትን እቃወማለሁ።

በአሁኑ ግዜ በሃይማኖት ስም መነገድ የተለመደ እየሆነ መጥቷል። አንዳንድ ቤተክርስትያኖች አዲስ አበባ ውስጥ በሱቆች ተከበው እንደሚገኙና እንደሚነግዱ ያልሰማችሁ አትኖሩም። አንዳንዶቹ ደግሞ በሱቅ በመከበባቸው የተነሳ መግቢያው ሰለሚዘጋ እንደ ደብረ ዳሞ በቅርብ ቀን በገመድ ተንጠልጥለን እንደምንገባ አልጠራጠርም።

ሌላው የሚገርመው ደግሞ በቅርብ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ የመጣ ሰው እንደነገረኝ ከሆነ በየቤተክርስትያኑ የቅዱሳንን ፎቶ መለጠፍ እየቀረ የጳጳስ ተብየውን ፎቶን ማንጠልጠል እየተገደዱ ነው። ይህንን ፎቶ ተመልከቱት ከአንድ ቤተክርስትያን የተነሳ ነው። በማርያም ፣ በጊዮርጊስ ምትክ ጳጳሱን ነው የምንመለከተው።




ይህንን ፎቶ ስትመለከቱት በየቤተክርስትያኑ የሚሰራውን ማሰብ ትችላላችሁ።በፖለቲካ ውስጥ እራሱን ከቶ የወያኔ ተወካይ የሆነው ጳጳስ የቅዱሶች መናህሪያ የነበረችውን ቤተክርስትያን ለውጦ በአዲሱ የገበያ ምጥኔ ሃብት የንግድ መአከል እያደረገው መሆኑን ያልተገነዘበ ህዝበ ክርስቲያን ይኖራል ብዬ አላምንም።

ስለጳጳሱ ቢወራ ቢወራ የማያልቅ ታሪክ አለ። በቅርብ ያረፉ እናታቸውን ለመቅበር ወደ አዲስ አበባ ከውጭ የመጡ አራት ግለሰቦች የጳጳሱን በቀብሩ ሰነሰርአት ላይ መገኘት በጣም ይፈልጉት ሰለነበርና በተወሰነው የቀብር ቀን ጳጳሱን ሰላልተመቻቸው የቀብሩ ቀን ማስቀየራቸው የከተማው ወሬ ሆኖ ሰንብቷል። ጳጳሱም በከተማው አሉ የተባሉ ሃብታሞች ከትኩስ እሬሳ እስከ መርዶ እንደሚደርሱ የታወቀ ነው።ዛሬ በአዲስ አበባ ያሉ ሃብታሞች ጳጳሱ ባልተገኙበት ዘመዶቻቸውን ከቀበሩ የተዋረዱና ክብራቸው የተነካ ይመስላቸዋል።በአዲስ አበባ ውስጥ ጳጳሱ በሚገኙበት የቀብር ስነስርአት ላይ አስከሬኑን ለማጀብ ጥቁር ማርሴዲስ ስለሚሰፈልግ የሚከራዩም ተዘጋጅተዋል።እንደሃብታምነቱ ቁጥሩ በዛ ማለት አለበት።

በተለምዶ ጳጳስ ለተከፋው ፣ ለተበደለው ፣ ለተራበው ፣ ለጠማው ቆሞ እግዜርን ሲማጽን ፣ ምዕመናንን ለመልካም ስራ ሲጋብዝ መታየት የነበረበት ሲሆን በየቤተክርስትያኑ አጠገብ የተኮለኮሉትን የኔ ቢጤዎች ከመጤፍ ባለመቁጠር የየሃብታሙ ለቅሶ አዳማቂና አረብራቢ መሆን ምንኛ የሚያሳዝን ነው።

አሁን ግን በነፃው ኢኮኖሚ ቤተክርስትያናችንን ሙሉ በሙሉ ወደ ንግድ መድረክነት መለወጥ የሚገባ አይመስለኝም። ምን አልባት የቤተክርስትያን አገልጋዮችን እራስን በራስ ማስቻል ሊባል ይችል ይሆናል። ግን ሁኔታው ከዛም በላይ ነው። በቤተክርስትያኑ መሪዎች እየሰሩ የሚከራዩትን ሱቆች ምን እንደሚኪሂድባቸው ልብ ብሎ ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ነግ ተነገ ወዲያ የኔ ቢጤዎቹ ወደ ቤተክርስትያኑ እንዳይጠጉ እንደሚደረግም ጥርጥር የለኝም።

ታዲያ ሃይማኖትን ለመልካም ተግባር ሳይሆን ለእርካሽ አላማ ማዋል ሁላችንም እንቢ አይሆንም ብለን የምንቃወመው መሆን ያለብን ነው። ጳጳሱ የተከበረውን ፣ ለሃገር አንድነት የቆመውን ሃይማኖት፣ በጎ ምግባርን መርሆ አድርጎ ያሳደገንን ሃይማኖት፣ ለተበደሉ፣ ለተገፉ እንድንቆም ፣ የሌሎች ችግር እንዲሰማን አድሮጎ ያሳደገንን ሃይማኖት ፣ የሌሎችንን ሃይማኖትን እንድናከብር ያደረገንን ሃይማኖት እንደፓራላማ ተመራጭ የራሳቸውን ፎቶ እያሰቀሉ ክብሩን ሊቀንሱት ባልተገባ ነበር። ገና በህይወት እያሉ እንደ ፃዲቅ እንዲመለኩ የሚፈልጉ ጳጳስ የነፃ ገበያ ጳጳስ እንጂ ያቺ የተከበረች ቤተክርስትያንን እንደማይወክሉ ግልጽ ነው፡፡

ስለኛ የሚስነብ ሁሉ በሰላም ይክረም

መጋቢት 2000